# ተስካር ጎስጓሽ ደፍተራ

*በላይነህ አባተ*(abatebelai@yahoo.com)

ሕዝብ በበሽታ፣ በችጋርና በባሩድ ያልቃል፤ ምእመን ላለቀው ሕዝብ ተስካር ይደግሳል፤ ደፍተራ እየዞረ ተስካሩን ይጎሰጉሳል። እንደ ጦቢያ ከተሞች ሁሉ በውጪ አገር ከተሞችም ተስካር ጎስጓሽ ደፍተራ እንደ ፍየል ይንጋጋል። በዋሽንግተን ዲሲ ሥር የሰደደ ተስካር ጎስጓሽ ደፍተራ "በሊቢያና በደቡብ አፍሪካ ለተሰው ሰማእታት የአርባ ቀን መታሰቢያ እናውጣ!" እያለ ይሰብካል። ልብ በሉ ደፍተራ ተስካር ጎስጉሶ እንጅ ተስካር ደግሶ ወይም አውጥቶ አያውቅም። ተስካር የሚደግሰውማ ሐዘንተኛ ነው። ተስካርን አሳምሮ የሚያወጣውማ በአጭበርባሪ ደፍተራ እንደ በግ የሚነዳው መከረኛ ምእመን ነው። አዎ ተስካር አውጪዎችማ እንባቸውን የሚያፈሱት፣ ደረታቸውን የሚደቁትና ፊታቸውን የሚልጡት እናቶቻችንና እህቶታችን ናቸው። እንደሚታወቀው ደፍተራማ መሐራ ዛቂ፣ ዘኬ ዘክዛኪ፣ ፍታት ፈትፋችና ተስካር ጎስጓሽ ነው።

አለቃ አካለ ወልድ ክፍሌ ተዝካርን መታሰቢያ፣ በዓል፣ መሥዋእት፣ ፀሎት፤ ተዘከረን ደግሞ ታሰበ፣ ትዝ አለ፣ ተወሳ፣ ተጠራ እያሉ ይተረጉሙታል። (፩) እንደ ሊቀብርሃን አድማሱ ጀምበሬና መላከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ያሉ የቤተክርስትያኗ ሊቃውንት ደግሞ ተስካርን በመታሰቢያና በቁርባን መልክ ይስሉታል። (፪-፫) ተስካር ክርስትያን ከአፀደ ሥጋ ወደ ወደ አፀደ ነፍስ ሲሸጋገር የሚታሰብበት ዝክር ነው። በዚህ መታሰቢያ ዝግጅት የሟች ዘመዶች፣ የማህበረሰቡ አባላትና ካህናት ሟች በአፀደ ሥጋ ሳለ ያከናወናቸው ተግባራት እያስታወሱ ያመሰግናሉ፣ ይጸልያሉ፤ በድግስ መልክ የቀረበውን ቁርባን በልተውና ጠጥተው የሞተውን ሰው ፈለግ ለመከተል ቃል ኪዳን ይገባሉ። በሌላ አነጋገር የቅዱሳን ተስካር የበላ ቅዱስ ሥራቸውን ያስታውሳል፤ የእነሱን ፈለግ ለመከተልም ቃልኪዳኑን በሚጎርሰው እንጀራ ጠቅልሎ ይጎርሳል። በሌላ በኩል ደግሞ በአረመኔዎች ተስካር የተገኘ አረመኔዎች በሳጥናኤል እየተመሩ የፈጸሙትን ግፍ እያስታወሰ የአረመኔነት "ቃልኪዳን"ን ያህያ ጆሮ እያስመሰለ ከድግሱ ጋር ይጎርሳል ማለት ነው።

ተስካር በተለምዶ እንደሚታመነው ሟችን ገነት ለማስገባት የሚደረግ ጸሎት ወይም የሚደገስ ድግስ አይደለም። ሰው ገነት የሚገባው በሥራ በተደገፈ እምነቱ እንጅ ተስካር ጎስጓሽ ደፍተራ አይኑንና ልቡን ሞሰብ ላይ ተክሎ በደሰኮረው ድስኩር ወይም እምነት የለሽ ባለንብረት በደገሰው የደላ ድግስ አይደለም። (፬) በሥራ ያልዋል እምነት የሞተ እንደሆነ ያዕቆብ አስተምሯል። (፭) መላከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ተዝካር የሚደረግለት ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ ላገለገለና ትእዛዛትን ለፈጸመ እንደሆነ፤ ተዝካሩ የሚደረገውም ለነፍሱ መድህን ይሆናል ተብሎ እንዳልሆነ አስተምረዋል። (፫)

እንደተዘገበው ወንድሞቻችን በሊቢያ የታረዱት ማተባቸውን ባለመቁረጣቸው ወይም ክርስቶስን ባለመክዳቸው ከሆነ በሥራ በተረጋገጠው እምነታቸው ገነት ገብተዋል ማለት ነው። ታዲያ ገነት ለገቡ ሰማእታት የዋሽንግተን ዲሲውም ሆነ የሌላው አገር ደፍተራ የተስካር እረጥ እረጥ አላማው ምንድነው? በተለምዶ እንደሚታመነው የተሰውትን አምላክ ኃጥያታቸውን ይቅር እንዲላቸው ለመጸለይ ወይስ ሊቃውንት እንደሚሉት እነዚህ ሰማእታት በምድር ሳሉ የከፈሉትን መስዋእትነት ለማስታወስና እንደነሱ ለእውነት ወይም ለክርስቶስ ለመስዋት ቃል-ኪዳን ለመግባት? የሙታንን ኃጥያት ለማስፋቅ ከሆነ ሰማእት ኃጢያቱን ለማስፋቅ ጸሎት ከተስካር ጎስጓሽ ደፍተራ ያስፈልገዋል ወይ? የሰማእትነት ገድላቸውን ለማሰብና የእነርሱን ፈለግ ለመከተል ከሆነስ ከአሳዳጆቻቸውና ከአስገዳዮቻቸው ጋር ቂጡን የገጠመ ሲኖዶስና ተስካር ጎስጓሽ ደፍተራ ለዚህ ብቁ ነወይ?

በበደኖ፣ በአጋዴን፣ በሲዳሞ፣ በጋሞጎፋ፣ በከፋ፣ በኢሉባቦር፣ በወለጋ፣ በአምቦ፣ በመተከል፣ በባህርዳር፣ በጎንደር፣ በአዲሳባ፣ በአለም በቃኝ፣ በቃሊት፣ በዝዋይና በሌሎችም ሥፍራዎች የዜጎች ደም ሲፈስ በባቄላ የታነቀውን ዶሮ ደፍተራ ደቡብ አፍሪካ የረገፉት ዜጎቻችን በምን ማንኪያ ትናጋውን ከፈቱት ይሆን? የነፍስ ትንሽና ትልቅ ይኖረው ይሆን? ኢትዮጵያ ውስጥ በየቀኑ የሚቃጠለው ነፍስ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከሚቃጠለው ነፍስ ያነሰ ይሆን? ደቡብ አፍሪካ በዜጎቻችን ላይ የሚተኮሰው ባሩድና የሚቀጣጠለው እሳት ኢትዮጵያ ውስጥ በንጹሐን ላይ ከሚረጨው ባሩድና ከሚያያዘው እሳት የከፋ ሆኖ ይሆን? ወይስ ደቡብ አፍሪካ ያለው አረመኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው አረመኔ ከፍቶ ይሆን?

በሲኖዶሱ ውስጥ የተሰገሰጉት ተስካር ጎስጓሽ አቡን፤ ጳጳሳት፣ መነኩሳትና ሌሎችም ደፍተሮች ለነፍሰ-ገዳዮች እየሰገዱ የሚኖሩ አይደሉም ወይ? ነፍሰ ገዳይ ገዥዎች ሲሞቱ ከእለት እስከ አርባና አመታት ወገባቸውን እየሰበቁ ፍታት እየፈቱ የተዘረፈ ንብረት የሚፈተፍቱ፤ ተስካር እያሉ የሙስና ዘኬ እሚዘከዝኩ፤ ክርስትያን ባለሆነ ነፍሰ-ገዳይ ተስካር ላይ ተገኝተው የአረመኔነት ጽዋና ቃልኪዳን የሚሰረብቁ ጉዶች አይደሉም ወይ? እነዚህ ተስካር ጎስጓሽ ደፍተሮች ዛሬም ሲወባሩ የሚውሉት ዜጎቻችንን ወደ ሊቢያ፣ ደቡብ አፍሪካም ሆነ ወደ በአረብ አገሮች እያሰደዱ ለአራጅ ከሚያስረክቡት ጭራቆች

ጋር አይደለም ወይ? ስለዚህ ከነፍሰ-ገዳይ ጋር ጽዋ እሚያነሳ ደፍተራ ሰማእታትን ለማስታወስ የእምነትስ ሆነ የህሊና ብቃት አለው ወይ?

የቀን ተቀን ትዝብቻችን እንደሚነግረን ተስካር ኅስጓሽ ሲኖዶስና ደፍተራ የአርመኔ ገዥዎችን ትእዛዝ እንጅ የመጽሐፉን ቃል ሲጠብቅ አይታይም። ተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ ተስካር እንዲደገስ ይቀሰቅሳል እንጅ ምእመናን የተሰደዱበትና የተሰውበትን ዋና ምክንያት ለመመርመር አይተጋም። ተመርምሮ ቢቀርብለትም አሳዳጆችንንና ገዳዮችን ለመገሰጽ የሚያስችል የእምነት ብቃትና ቀጥ አድርጎ የሚያቆም ኅብለ-ሰረሰር የለውም። የገደሉትንና ያስገደሉትን ገስጥ ሲባል "ይህማ ፖለቲካ" ነው ይልና በነፈሰ-ገዳዮች ካብ ውስጥ እንደ እንሽላሊት ይሹለከለካል። አጥብቆ ጠያቂ ዘወር ሲል ምላሱን አስልቶ እንደገና ብቅ ይላል። የተስካር ድግስ ባጣጣመበት ምላሱና በኅሰኅሰበት ላንቃው "ፈሪሳውያን በሐሰት ከሰው መሰከሩበት፣ ጲላጦስ እጁን ታጥቦ ፈረደበት፣ አረመኔዎች ሰቅለው በጦር ወጉት" እያለ የደመወዝና የዝክርት መበያ ሰበካውን እሁድ-እሁድ ይሰብካል። "በሄሮድስ ዘመን የነበረው ግፍ አሁንም በጦቢያ እየተፈጠመ ነው። አቃቢ ሕግ እሚባለው ፈሪሳዊ የውሸት ምስክር እያሰለጠነ በጲላጦሳዊ ዳኞች አስፈርዶ እውነተኞችን እያሰቃዬ በመግደል ላይ ነው" ሲባልም "እዚህ ውስጥ አልገባም፤ ይህ ፖለቲካ ነው" እያለ በአስራት ከፋዩ ምእመናን ነፍስ ቀልዶ ይሸሻል። ራቁቱን ቅቤ ተቀብቶ እንደሚሰርቅ ሌባ አሙለጭልጮ ሊያመልጥ የሚሞክረው ይህ ተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ አትግደሉ፣ ሕዝብን አታሰቃዩ፣ አትስረቁ፣ ለገንዘብ አትገዙ፣ አትቅጠፉ፣ በሐሰት አትመስክሩ፣ በአድሎ አትፍረዱ የሚለውን ክርስቶስም ፓለቲከኛ ሆንክ ብሎ አፉን ይዘጋው ይሆን?

ተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ ገዳይን አትግደል የሚያሰኝ የክርስቶስ ጸጋ ባይኖረውም አረመኔ ገዳይ የገደላቸውን ክርስቲያኖች ፍታት የሚፈተፍትበትና ተስካር የሚኅሰጉስበት ሰፊ አፍ አለው። ሄሮድሳዊ ገዥ፣ ይሁዳዊ ሰላይ፣ ፈሪሳዊ አቃቤ-ሕግ፣ ጲላጦሳዊ ዳኛ፣ ነገር አመላላሽ ካድሬና አረመኔ ታጣቂ እንዳያዩው ተደብቆ የተገደሉትን ፍታትና ተስካር ሊኅሰጉስ በካባ ተቦጅኖና መስቀሉን ጨብጦ ሰፈር ለሰፈር ይርመሰመሳል። አቡነ ዘበሰማይትን ይደሰኩርና ሆዱን እንደ ፊኛ ይወጥራል፤ ጸበሉን ይረጭና ኪሱን እንደ ኳስ ያሳብጣል።

ካማረው የፍታትና የተስካር ድግስ ላይ አይኑን ተክሎ ከሀዲው ተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ ስለ ሳጥናኤል አሳሳችነትና ስለ ይሁዳ ክህደት ይሰብካል። ያዕቆብ "ቃሉን የምታደርጉት እንጅ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ (ያዕ ፩:፳፪)ያለውን ደልዞ እርሱ ገንዘብና ስልጣንን እያመለከ ከእግዚአብሔር በቀር በሌላ አታምልኩ፤ እርሱ ሲያታልል እየዋለ በሐሰት አትመስክሩ፤ እርሱ ሲያመነዝር እየዋለ አታመንዝሩ፤ እርሱ ከገዳይዎች ጋር እየዋለ አትግደሉ፤ እርሱ በኅሳ ከሚያጋጩና ሲኖዶስን ከከፈሉ ወሮበሎች ጋር እየተሞዳሞደ ባለንጀራህን እንደራስህ አርገህ ውደድ እያለ መከረኛውን መስቀል ጨብጦ ይሰብካል። የዋሁ ምእመንም ግብሩን ሳይሆን ለማጭበርበር እንደ ኮፍያ ያጠለቀውን ቆብ፣ እንደ አውሎ ነፋስ የቆለለውን ጥምጣም፣ እንደ ካፖርት የተለበደበትን ካባ፤ ለማታለያ የጨበጠውን መስቀል እየተመለከተ ለእርድ እንደሚሳብ በግ ይከተለዋል። በተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ የሚኅተተው ሰበበኛ ምእመን እግዚአብሔር ክፉና ደጉን እንዲለይበት በተሰጠው አእምሮ ይተኛና "እግዚአብሔር ይቅጣው" እያለ ኃላፊነቱን መልሶ ለእግዚአብሔር እየሰጠ ከተስካር ኅስጓሽ ሲኖዶስና ደፍተራ ጋር መጓተቱን ይቀጥላል።

አንድ ቀልደኛ ጎበዝ የመሪጌታ ልጅ የሆነውን አብሮ አደጌን "ላንተ አባት ሰው በምኑም በምኑም ሲረግፍ  ለቆ ይጥልለታል ሲል ቀለደበት። ( ለቆ የበልግ ዝናብ መዝነብ ሲጀምር አገፍግፎ ሲወጣ ከብቶችን የሚያስደስት ሳር ማለት ነው።) አባትህ የፍታትና የተስካር ድግስ ሲደገስ ደስ ይለዋል ማለቱ ነበር። አዎ ይህ አባባል  ቀልድ ነበር። የአብሮ አደጌ አባት ዛሬ እርጅና ተጭኗቸው አግልኅሎታቸው ቀነሰ እንጅ እውነተኛ ካህን ነበሩ። በግብር ክህነታቸውን አሳይተዋል፤ ስንቱን ሊቃውንትም አስተምረዋል። ለዛሬ ዘመን ተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ ግን ይህ የለቆ ብሂል እውነትነት አለው። የሕዝብ እልቂት ለዛሬ ዘመን ተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ ለቆ ይጥላል። በሊቢያ፣ በየመን፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በበደኖ፣ በአሩሲ ነገሌ፣ በጋንቤላ፣ በኦጋዴን፣ በወለጋ፣ በመተከል፣ ባዲሳባ፣ በጎንደር፣ በባህርዳር፣ በከፋ፣ በሲዳሞና በሌሎችም ቦታዎች ሕዝብ በግፍ ሲያልቅ ድሃ እናቶች ጥሪታችውን ሙጥጥ አያደረጉ በኩበት ጪስ እየታጠኑ ፍታትና ተስካር ይደግሳሉ። ይህ እልቂት ከኢትዮጵያም አልፎ በውጪ ለሚገኝ ተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ የፍታትና የተስካር ለቆ ጥሏል። ይህ የፍታትና የተስካር ለቆ በዋሽንግተን ዲሲም ዘነበ ተብሏል። በየካንቦው ያሉ ተስካር ኅስጓሽ ደፍተሮችም ሕዝቡ ተስካር እንዲያወጣ በአርባ ቀን መታሰቢያ ወረቀት ጠርተውታል። እንግዲህ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ሕዝብን ከፋሽሽት ጭፍጨፋ ላማዳን ከሚጋፈጥ ሳይሆን ከፋሽሽቶች ጉያ ተደብቆ ፋሽሽቶች አሰድደው ያስፈጁትን ምእመናን ተስካር ለመኅስኅስ ገዳምን ትቶ ካምቦ ውስጥ ከሚተም ቆመስ፤ መነኩሴና ደፍተራ ምን ቁምነገር ይጠበቃል?

ምእመን ሆይ! ገዳይና አስገዳይን የማይገስጽ፣ ለእውነትና ለፍትህ የማይቆም፣ ለተስካር ግን እሚሽቀዳደም ተስካር ኅስጓሽ ደፍተራ እንደ አጭበርባሪ ፈረንጅ "በልሳን አድናለሁ" እያለ ቮድካ እያንደቀደቀ ከሰው ሚስት ጋር ከሚያድረው(፮) አለዚያም አጋባለሁ ብሎ ሙሽራዋን አማሎ ከሚነጥቀው ፓስተር(፯) በምን ይለያል? የሰው ሚስት ነጣቂው ፓስተርና

ተስካር ኀስጓሽ ደፍተራ በግብራቸው ከዲያብሎስ በምን ይለያሉ? ዲያብሎስ "ዳብዬ እባላለሁ" እያለ እራሱን እያስተዋወቀ ይመጣል ወይ? ታዲያ የዲያብሎስን ግብር ከሚያራምድ ተስካር ኀስጓሽ ደፍተራ ተሰጥኦን ተቀብሎ እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ይቻላል?

ነፍሳቸውን ይማርና አለቃ አያሌው ታምሩ በቁማቸው የፈቷቸውን ከነፈሰ-ገዳዮች ጋር የቆሙ አቡንና ጳጳሳት ሲሞቱ እንዳይፈቷቸው ተናዘው ነበር ይባላል። እኛስ ከነፈሰ-ገዳዮች ቤት እግራችውን ተክለው ገንዘብ ለመሰብሰብ እጃቸውን ወደ እኛ የዘረጉትን ተስካር ኀስጓሽ ደፍተሮች ገፍትረን የምንጥለው መቼ ነው? የገዳዩንም የተገዳዩንም ተስካር እየዋጡ ከሚሰዋውም  ከተሰዊም ጋር የሚቆርቡትን የአቡን፣ የጳጳስ፣ የቆመስ፣ የመነኩሴ፣ የቄስና የዲያቆን ደፍተሮች ከመቅደሳችን የምናባርረው መቼ ነው? በማቴዎስ ፮፡፳፬ና በሉቃስ በ፲፮፡፲፫ ለሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም ብሎ የተጣፈውን ፍቀው ለሆዳቸው ሲሉ የገዳዩንም የሟቹንም ፍታት የሚፈተፍቱና ተስካሩንም የሚኀሰጉሱ ተስካር ኀስጓሽ ደፍተራዎችን እንደ አረም ነቅለን እንደ ድሮው ከእውነተኛ አባቶች ጋር እግዚአብሔርን ማምለክ የምንጀምረው መቼ ነው? በእምነተ-ቢስ አረመኔ ገዥዎች ተሰብሮ አስመሳይ፣ አድር-ባይ፣ ቀጣፊና አጭበርባሪ ተስካር ኀስጓሽ ቆመስ፣ መነኩሴና ደፍተራ እንዲገባበት የተደረገው የቤተ-ክርስትያናችን አጥር የሚደፈነው መቼ ነው? ተስካራችንን የሚኀሰጉሱ ሳይሆን እንደ አቡነ ጴጥሮስ ራሳቸውን አሳልፈው የሚሰጡልን የክርስቶስ ተከታይ አባቶች የምናገኘው መቼ ነው?

አምላክ ሆይ! አለምን የወደደ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ ነው (፰) ያልከውን ተገንዝበን በጥቂቱ እንኳን አለምን ንቀን ከአንተ እንድንታረቅ ልቡናችንን ክፈትልን። ከነፍሰ-ገዳዮች ጉያ ተደብቆ ተስካራችንን ሊበላ የአርባ ቀን መታሰቢያ ከሚሰብክ  የአቡን፣ የጳጳስ፣ የመነኩሴ፣ የቆመስ፣ የቄስና የዲያቆን ተስካር ኀስጓሽ ደፍተራ ገላግለን። አለምን ንቀውና ከአንተ ተፋቅረው በጎቻቸውን ተግተው የሚጠብቁ እረኛ አባቶች አውርድልን። አሜን።

**ዋቢ፡-**

፩. አለቃ አካለ ወልድ ክፍሌ፡-የግዕዝና አማርኛ መዝገበ ቃላት
፪. ሊቀብርሃን አድማሱ ጀምበሬ፡-ተዝካርና ዝከር፤ ኮኩሐ ሃይማኖት ገጽ ፪፻፹
፫. መላከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ፡-ተዝካር የሃይማኖት አበው ኮሌጅ ተማሪዎች መጽሔት ሐምሌ ፭ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ገጽ ፺፰-፺፱
፬. የያዕቆብ መልእክት ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው። ፪፡፲፯-፳፯
፭. የያዕቆብ መልእክት "ቃሉን የምታደርጉትን እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ ፩፡፳፪
፮. የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ፡-የሰው ሚስት ስለደፈረው ፓስተር http://www.zehabesha.com/voa-special-report-sexual-abuse-allegations-pastor-tekeste-getnet/
፯. ፓስተሩ ትዳሬን አፍርሷል፤ ሚስቴን ቀምቷል፡- EMF, Amharic May 24, 2015 (Gregorian) ፰. ማቴዎስ ወንጌል ፮፡፳፬
፱. የሉቃስ ወንጌል ፲፮፡፲፫
፲. የያእቆብ መልእክት፡- የአለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል ያዕ ፬፡፬-፭

**ተመሳሳይ ጽሑፎች፡-**

*፩ ድንጋይን የሚያናግረው ውኃ ነው http://www.abugidainfo.com/amharic/wp-content/uploads/2012/12/dengay-21.pdf*
*፪. አባ ባህሩ ናፈቁኝ http://addisvoice.com/amh/AbaBahiru.pdf*
*፫. ኮፍያ እንበልሽ ባርኔጣ http://www.abugidainfo.com/amharic/wp-content/uploads/2011/12/barnetta.pdf*
*፬ ምንድነው ምንኩስና http://www.abugidainfo.com/amharic/wp-content/uploads/2010/11/minkussina-1.pdf*
*፭. ሰማይ አይታረስ ካህን አይከሰስ http://www.abugidainfo.com/wp-content/uploads/2014/08/kahin.pdf*
*፮. ስም አውጡልኝ http://www.abugidainfo.com/amharic/wp-content/uploads/2010/05/sim_awutu.pdf*
*፯. ብጹዓንና ቅዱሳንን ያያችሁ! http://www.abugidainfo.com/amharic/wp-content/uploads/2013/04/qiddusan-1.pdf*
፰. ድንጋይ ዳቦ ብሎ መጥራት ይብቃን http://addisvoice.com/wp-content/uploads/2014/10/dingayn-dabo-malet-yibkan.pdf
፱. የስኳር በሽታ ቤተክርስትያንን አጥቅቷታል፡- http://www.abugidainfo.com/amharic/wp-content/uploads/2014/12/sugar.pdf
፲. አእምሮ ኢትዮጵያ ገደል አፋፍ ላይ፡-http://www.abugidainfo.com/amharic/wp-content/uploads/2015/01/Aemero-Ethiopia-1.pdf

*ሰኔ ሁለት ሺ ሰባት ዓ.ም.*